# መጥተህም፡ ተከተለኝ

እንደሱ፡ አይደለም፡ ይህ የሆነው ቤኪ ከመወለዷ በፊት ነበር። ስለዚህም እ—እንዲህ አሰብኩ፡ “መልካም፡ ታውቃላችሁ… ” የአስር ሳንቲም፡ አ—አንድ ሰሃን ሙሉ ኦትሚል በላሁ። መልካም፡ ቲኬት ሰ… ሰጡኝ፡ ፈረምኩበት፡ አያችሁ፡ የወጪ ሂሳብ ስለነበረኝ፡ ከፈልኩት፡ መልሼ ሰጠሁት፡ እና አስገባሁት።

2 አንድ ቀን ደግሞ የ—የአካባቢ ጥበቃ ሰራተኞች ሰብሰባ በነበረን ጊዜ። “ማይ፡” እንዲህ አሉ፡ “እንዲህ ያለ ነገር የመለሰው ይህ እብድ ማን ነው? ” አያችሁ? ታ—ታውቃላችሁ፡ ዋናው ሰውዬ፡ “ለቁርስ አስር ሳንቲም? ” ታውቃላችሁ፡ ስለዚህ ከሌሎቹ ይልቅ የኔ በጣም ርካሽ ነበር። አንዳንዶቹ አንድ ዶላር አቀረቡ፡ አያችሁ፥ ሁለት ዶላር ለአራት አቀረቡ። እኔ ደግሞ ትክክለኛውን ዋጋ ተናገርኩ።

3 መልካም፡ እንዲህ አልኩ፡ “መልካም፡ አሁን፡ ያንን መመለስ አያስፈልግም… የበላሁት የአሥር ሳንቲም ብቻ ከሆነ፡ ምን አደርጋለሁ? ”

4 ረዳት ተቆጣጣሪ የነበረ፡ ሚስተር ፊልድስ፡ “ቢሊ፡ ለማንኛውም፡ ቢያንስ፡ አንድ ዶላር አቅርብ፡” አለኝ። “ሌሎቹ እያደረጉት ይህንኑ ነው፡” አለኝ። “አንተም ከእነርሱ ጋር አንድ ማድረግ አለብህ፡” አለኝ።

5 “መልካም፡” እኔም “የበላሁት—አንድ ሰሃን ኦትሜል ብቻ ነው፡ የከፈልኩትም ያ ብቻ ነው፡” አልኩት።

“ኦህ፡ እንዲህ አታድርግ፡ በጭራሽ እንደዚህ አታድርግ፡” አለኝ።

6 እና፡ “በዚህ ገንዘብ ምን ላድርግበት? ” ብዬ አሰብኩ፡ ለቁርስ ኀምሳ ሳንቲም አስከፈልኩ። ከዚያም አርባ ሳንቲም አስቀረሁ፡ በዚያም ምንም ማድረግ ብፈልግም፡ በመንገድ ላይ ላሉ አንዳንድ ልጆች ሰጠኋቸው፣ አንዳንድ ልጆች፡ ታውቃላችሁ፡ ትንሽ ሳንድዊች ለሚያስፈልጋቸው፡ ለሌሎች ሰጣኋቸው። መልካም፡ ምናልባት… እንዲህ ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ በትክክል፡ ኩባንያው፡ ራሱ፡ ያነጋገረኝ ሆኖ ተሰማኝ። እርሱ ግን ከኩባንያው ውጪ ነበር።

ስለዚህ፡ “ምናልባት—ስህተት ሰርቻለሁ፡” ብዬ አሰብኩ።

7 ስለዚህ እዚህ በቅርብ ጊዜ፡ ከአንድ የአካባቢ ጥበቃ ሰው ጋር… አሁን ቁጥጥር ሲያደርጉ በሆሊኮፕተር ሆኗል፡ አያችሁ። ስለዚህ አጠገቤ መጥቶ ቆመ። እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አለኝ፡” “ይህ ዛፍ’ኮ አደገ፡” አለኝ።

እኔም “አዎን፡” አልኩት። “ልጆች ከሰሩ ይጫወታሉ፡” አልኩት።

እርሱም “እናስተካክለው እንዴ፡” አለኝ?

“ይቻላል፡ ግን በደንብ አትቁረጡት። እሺ? ” አልኩት፡

እርሱም “አይ፡ ልንቆርጠው ፈልገናል። ዋጋውን እንከፍልሃለን፡” አለኝ።

8 እኔም “አይ። አይ። እንድትቆርጡት አልፈልግም፡” አልኩት። መልካም፡ እኔም፡ የመንገድ-መብት-ህጎችን አውቃለሁ፡ ታውቃላችሁ፡ ምክንያቱም ሰባት

ዓመት በዛ ላይ ሰርቻለሁና። “አይሆንም፡” አልኩት። እኔም “እንዲቆረጥ አልፈልግም፡ ከላይ ማስተካከል ግን ትችላላችሁ፡” አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ “ሁሌም ከ—ከላይ አስተካክለዋለሁ፡ ግን፡” “ከፈለግክ ትችላለህ። ከላይ ማስተካከል ትችላለህ፡” አልኩት። እኔም፡ “እኔ፡ ወንድም ዉድ እና እኔ፡ መንጥረን ልናስተካክለው ነበር። እነዚህን ሁሉ ሌሎች እዚህ ጋር ያሉትን አስተካክለናቸዋል” አልኩት። እንዲህ አልኩ፡ “ይህንን ግን ለልጆች ሰንል እዚያ ማቆየት እንፈልጋለን፡ እነ ጆ እና ሌሎች፡ ታውቃለህ፡ በዚያ ዛፍ ስር የሚጫወቱ ትናንሽ ልጆች አሉ።”

9 ጉዞ ሄጄ ነበር። ተመልሼ ስመጣ፡ በመጋዝ ተቆርጣ በቦታዋ አልነበረችም። ኦህ፡ ያንን ዛፍ በመቁረጡ ምክንያት፡ በኩባንያው ላይ፡ ምን ዓይነት ክስ ሊሆን እንደሚችል፡ ታዩታላችሁ። እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “አሁን፡” እንዲህ አልኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ ያንን ማንሳት እንኳ አልፈልግም።” እያችሁ? “በምንም ነገር ውስጥ፡ ቢ—ቢሆንም፡ አንዳንድ ጊዜ፡ አሰር ሳንቲም ብቻ የወጣ ነገር ብበላም፡ ‘ኀምሳ ሳንቲም’ መመለስ አለብኝ።’ እያችሁ? እንዲህ አልኩ፡ “በዚህ ጉዳይ ላይ ችግር ካለ፡ በዚህ ይተካልኝ፡ እያችሁ፡ ያ—ያንን—ያንን ወጪ ጨምሬ መለስኩት፡ እያችሁ። ያም እኔ... ” ከዚያ በኋላ የመንግስት ኩባንያ ቅጥር ሰራተኛ መሆን አስጠላኝ፡ እያችሁ፡ ምክንያቱም ከበስተጀርባ የሆነ ነገር አለበት።

ምን እንደምናደርግ መጠንቀቅ አለብን። አንድ ቀን ዋጋችን እንቀበላለን።

10 ልጆች፡ እዚህ እየመጣችሁ። እናታችሁ፡ ትሩዲ፡ በቀደም እዚህ ነበረች። አላወቃችሁም፡ ብዬ እገምታለሁ። ይህ ሳርፕራይዝ እንደሆነ፡ ተረድቻለሁ። አሁን በቅርብ ትመረቃላችሁ። ከዚህ በፊት አብረን ጉዞ አድርገናል። ከስብሰባው በኋላ፡ ወዲያውኑ ወደ ሰብሰባ እሄዳለሁ። ወደ ቤትም እንሄዳለን።

11 ለሁላችሁም ለመናገር ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነ አሰባለሁ፡ ከዚያም ደግሞ ከመመረቃችሁ ትንሽ ቀደም ብሎ ከልጆቹ ጋር መነጋገር ጥሩ እንደሆነ አሰባለሁ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጥቅስ አነብና፡ ለአሰር ደቂቃ ያህል፡ ከልቤ ለእናንተ እናገራለው። ከዚያም ከመንገዳችሁ ፈቀቅ እላለው። እያችሁ?

12 ለልጆቹ ከመናገሬ በፊት፡ ለአዋቂዎች፡ እንዲሁም ለሁላችሁ፡ ለአንድ ደቂቃ መናገር እፈልጋለሁ። አሁን፡ ምናልባት፡ ያደረግነው ጉዞ፡ ምናልባት አድካሚ ነው። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተማርኩትን ተሞክሮ፡ እዚህ ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ለተማርኩት አሥር ሺህ ዶላር አልወሰድም። በእርግጥ ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ በመታዘዝ እንደመጣሁ አምናለሁ፡ ለ—ለዘላለምም እንደዛው መቈየት እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ። እናም...

13 ስመጣ ሳለሁ፡ በራእይ፡ አንድ ነገር ሲሆን አየሁ፡ ከቱክሶን በላይ ቆሜ እ—አንድ—አንድ ፍንዳታ ፈነዳ። እና፡ ይህ ሲሆን ወንድም ፍሬድ በቦታው ነበር። እና ያንን ፎቶ፡ ታውቃላችሁ፡ ከሰማይ ላይ አንስተውታል። ስለሱም ብዙም አላሰብኩበትም ነበር፡ በጭራሽ አላስተዋልኩም ነበር። ስለዚህ ሌላ ቀን ላይ፡ በሆነ መንገድ ያሰደነቀኝ ጀመረ። ወንድም ኖርማን፡ የኖርማ አባት፡ ነገረኝ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ይህንን አስተውለኸዋል? ”

14 ልክ እንዳየሁት፡ መላእክቶቹ በሰዕሉ ላይ በግልጽ ይታዩ ነበር፡ በጣም ግልጽ ነበሩ። አያችሁ? ጊዜው መቼ እንደሆነ ለማየት ተመለከትኩ፡ ጊዜው፡ ልክ ነበር፡ ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በፊት፡ ወይም እዚያ ከነበርኩ ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ ነበር። የት እንደነበረ ተመለከትኩ። "ከፍላግስታፍ በሰተ ሰሜን ምሥራቅ፡ ወይም ፕሪስኮት፡ ይህም ከፍላግስታፍ በታች ነው።" እና፡ ልክ እኛ በነበረንበት ቦታ ነበር፡ አያችሁ፡ በትክክል እዚያው ነበር።

15 "ሃያ-ስድስት ማይሎች ከፍታ ላይ።" ለምን፡ ትነት ከ—ከአራት ማይሎች በላይ መሄድ አይችልም፡ እርጥበት፡ ወይም ማንኛውም ዓይነት ጭጋግ ወይም ማንኛውም ነገር ከአራት ማይሎች፡ ወይም አምስት በላይ፡ አይሄድም፡ አያችሁ። አውሮፕላኖች በአሥራ ዘጠኝ ሺህ ከፍታ ይበርራሉ። ይህ ከደመናዎች ሁሉ በላይ ለመውጣት ነው፡ አያችሁ። አሥራ ዘጠኝ ሺህ ማለት አራት ማይሎች ያህል ከፍታ ነው። ሰዕሉን አይታችሁ ከሆነ፡ ሀያ-ስድስት ማይል ከፍታ፡ ዙርያውም ሠላሳ ማይሎች፡ የፒራሚድ ቅርጽ ነበረው።

16 እንደነገርኳችሁም፡ በቀኝ-በኩል፡ ድንቅ፡ መልአክ፡ አስተዋልኩ። እነሆ፡ በቀጥታ ሲመጣ፡ ደረቱ ወጣ ብሎ፡ ክንፎቹ ወደ ኋላ ሆነው፡ ልክ በመጀመሪያ እንደነበረው ነበር። በመጀመሪያ አላስተዋልኩም ነበር… በጣም ብዙ ነገሮች ነበሩ።

17 በቀደም በመንገድ ላይ እየመጣሁ ሳለ፡ የሆነ ነገር ማድረግ ያለብኝ—ነገር ምን እንደሆነ ተናገረኝ። የ—የእኔ መልእክት አይደለም።

18 በአንድ ወቅት፡ ሊዮ ሜርሲየር እንዲህ ብሏል፡ እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ጊዜው ከዚህ በኋላ ይመጣል፡" ከአምስት ወይም ከሰድስት ዓመታት በፊት፡ ምናልባትም ከሰባት ዓመታት በፊት፡ እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ጌታ አገልግሎትህን ይለውጠዋል፡" አለኝ። እንዲህም አለ፡ "ይህን ሲያደርግ፡ ምናልባት የሆስፒታል በሽተኞችን አሰልፈህ፡ ከአልጋዎቻቸው እና ከ—ነገሮቻቸው እንዲወጡ ትናገራለህ" አለኝ። ምንም እንኳን ወንድም ሊዮ በቅንነት ለመናገር እየሞከረ ነበር የሚል እምነት ቢኖረኝም፡ ትክክል አልመሰለኝም።

19 ትክክል ግን አይመስልም፡ ምክንያቱም፡ አያችሁ፡ ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ አላደረገም። አያችሁ? ወደ ሆስፒታሎችም ሄደ። በዚያ ሆስፒታል ውስጥ አንድ ሰው ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የት እንደነበረ ታስታውሳላችሁ? የቤተ ሳይዳ መጥመቂያ። በዚያም ሽባዎች፡ አንካሶች፡ ዕውሮችና፡ ሽባዎች፡ የሆኑ እጅግ ብዙ ሰዎች ተኝተው፡ መልአኩን ይጠባበቁ ነበር። አሁን፡ ይህ የሆነው ሰዎች መለኮታዊ ፈውስ ለማግኘት በሚጠባበቁበት መንፈሳዊ ሆስፒታል ውስጥ ነበር። እዚህም መለኮታዊው ፈዋሽ ራሱ ገብቶ አንድን ሰው ፈውሶ ወጣ። ስለዚህ አንድ ሟች ሰው፡ ወይም የሚመጣው አገልጋይ፡ ከዚህ የበለጠ ይሆናል ብሎ መጠበቅ አይቻልም። አያችሁ? በዚህ መስማማት አልቻልኩም።

20 ነገር ግን ላለመስማማት ሰሞክር፡ መንፈስ ቅዱስ በእኔ ላይ መጣ። ሊዮ ብዕር ካለው ጠየኩት። ቁራጭ ወረቀት ወሰጄ፡ ጻፍኩት። እሱ ያለበት ቦታ ከሄዳችሁ፡ በተሳቢው ቤት ውስጥ ይገኛል። የዕቃ ማመላለሻዬ የነበረው አሮጌው የአሉሚኒየም ተሳቢ ቤት ነው። ልክ በበሩ ስትገቡ፡ በቀኝ-በኩል

አንድ መደርደሪያ አለ፡ በተሳቢው ቤት ፊት ለፊት። ከታች ተቀምጧል። እዚያ ላይ አስቀመጥኩት። እንዲህ አልኩ፡ “አንድ ቀን ይህን ማውጣት ትችላለህ። ‘እግዚአብሔር አገልግሎትን አይለውጥም፡ ነገር ግን አገልግሎቱን የያዘውን ሰው ይለውጣል አለ።’” መደረግ ያለበት ይህ ነው።

21 አያችሁ? ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ፡ ግን—ማድረግ—አልችልም፡ አሁን ባለሁበት ሁኔታ ይህን ማድረግ አ—አልችልም። ምክንያቱም፡ በ... በውስጤ የሆነ ነገር መሆን አለበት፡ ይህም እግዚአብሔር እንዲሠራው የሚያደርግ ነገር ነው።

22 ወደ ቤታችን ለመመለስ እያሰብን ነው። ልጆች ቤት ናፍቆአቸዋል፡ ሁሉም ወደ ቤታቸው መመለስ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ጌታ ቢፈቅድ፡ ምናልባት፡ ከቅዳሜ አገልግሎት በኋላ፡ ይዤአቸው ለመመለስ እያሰብኩ ነው። ከዚያ በኋላ ግን፡ አላውቅም። ያ ነገር በውስጤ በሚሆን ጊዜ ወዲያውኑ፡ አሁን ከማደርገው የተለየ፡ ለሰዎች ልዩ የሆነ ስሜት በውስጤ እንዲኖር እንደምያደርግ አውቃለው። ሕዝቡን ተቃውሜ ነበር፡ አያችሁ፡ ከእነሱ ጋር ምንም ግንኙነት እንዲኖረኝ አልፈለግሁም ነበር። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ታውቃላችሁ፡ **ሪኪ፡ ሪኬታ** ብዬ የምጠራውን፡ እነሱ የፈጸሟቸው ነገሮች ነበሩ። በቅንነት ሰበክሁ፡ እግዚአብሔርም በሁሉም መንገድ አረጋገጠው። “ማመን የማይፈልጉ ከሆነ፡ በቃ፡ ተዉአቸው።”

23 በመጪው መኸር ከነ በድ ጋር ለመገናኘት፡ በዚያም ድንኳን ለመትከል፡ ወደዚያ እሄዳለው። ፀጉሬና ጢሜ እንነሰኪያድጉ ድረስ፡ በምድረ በዳ ውስጥ እቆያለሁ። ጌታ ወደ የትኛውም ቦታ እንድሄድ ከፈለገም፡ አንድ ቃል ይልክልኛል፡ ወርጄም ያለኝን አደርጋለው።

24 እና በመንገድ ላይ፡ በቀደም እየመጣሁ፡ አቆመኝ። ወደ ምን እ... እየመጣሁ እንደሆነም አየሁ። አሁን ወደ—ሌላ ነገር እየተጓዝኩ ነው። ወደ ቤት ስመለስም፡ ልብ-ለ-ልብ ብለን የምንጠራውን ንግግር አደርጋለሁ፡ ብዬ አሰብኩ፡ ምናልባትም በቴፕ ላይ እንቀዳዋለን፡ ከዚያም ሕዝቡ ለምን ድንገተኛ ለውጥ እንደሆነ ይመለከታል።

25 አሁን፡ እናንተ ልጆች፡ እስኪ ትንሽ... ጸሎት እንጸልይ።

26 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ወጣቶች እና አዛውንቶች፡ እና በመካከለኛ ዕድሜ ውስጥ ያለን ሁላችንም፡ እንደተሰበሰብን በማወቃችን፡ በዚህ-ጊዜ እናመሰግናለን። ስለዚህ ዘላለማዊ ነገር፡ ስለ አንተ፡ እና ስለ ዘላለማዊ ህይወት የሚመለከቱ ነገሮችን ለመናገር እንደገና ተሰብስበናል።

27 እናም ዛሬ ምሽት እዚህ የተቀመጡት ወጣቶች፡ አንዳንዶቹ አሁን የሚመረቁ፡ አንዳንዶቹም አስቀድመው የተመረቁ ናቸው። ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ ከቱክሰን በስተ ሰሜን በሚገኘው ተራራ ላይ የጌታ መላእክት ሲወርዱ፡ ታላቅ ርዕደ መሬት፡ ወይም ታላቅ ፍንዳታ ከመከሰቱ፡ ከጥቂት ሰዓታት በፊት፡ የሆነ አንድ ነገር እንዳለ ተገንዝቤያለው። የተነገረውን አስታውሳለሁ፡ በ—በተለይ ስለወጣቶች የተባለውን። ጌታ ሆይ፡ እንድንረዳው እንድታግዘን፡ እጸልያለው። እናም ዛሬ ማታ፡ ለእነዚህ ወጣቶች፡ በጉዞው ላይ የሚረዳቸው አንድ ነገር መናገር እንድችል አግዘኝ። ጌታ ሆይ፡ በዚህ ጊዜ ሁላችንም፡ እርዳታ እንፈልጋለን።

28 አንድ ላይ ባርከን። ኃጢአታችንን ይቅር በለን። እዚህ ከመጣንበት ጊዜ አንሥቶ፡ ያደረግነው ማንኛውም ነገር ቢያሳዝንህ፡ ይቅር አድትለን እንጸልያለን። ለ—ለነገ ምንም ዋስትና፡ እንደሌለን ዛሬ፡ ተገንዝበናልና። ነገ ምን እንደሚያመጣ አናውቅም። ነገን ለመገናኘት ዛሬ መዘጋጀት አለብን። እናም፡ አባት እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህን ለማድረግ የምናውቀው አንድ መንገድ ብቻ ነው፡ ይኸውም፡ አንተን ለመገናኘት መዘጋጀት ነው፡ ምክንያቱም ቀስ በቀስ ሁላችንም ይህን እንደምናደርግ እንገነዘባለን። እናም አንድ ጊዜ በሰላም፡ እንደ ጓደኛ፡ ወይም ልጅ፡ ወይም እንደ ጠላት እንገናኛለን። የተወደድን ልጆችህ ከመሆን በስተቀር ሌላ ማንኛውንም ነገር፡ ይራቅ፡ ጌታ ሆይ። እነዚህን የምንጠይቃቸውን ነገሮች፡ በኢየሱስ ስም ስጠን። አሜን።

29 ዛሬ ጠዋት፡ እረኞችን እያረምኩ ሳለሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ አንድ ቦታ አገኘሁ፡ በዚህ ሰዓት ማንበቡ ጥሩ ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ምናልባት... በጣም ተገቢ ላይሆን ይችላል፡ ነገር ግን... ለ—ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ፡ ለመነጋገር አሰብኩ። ይህንን ከቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ላይ ማንበብ እፈልጋለሁ። አራቱም የወንጌል ጸሐፊዎች ስለዚህ ጉዳይ ጽፈዋል። ምዕራፍ 18 እና 18 ኛ ቁጥር።

> **ከአለቆችም አንዱ፡ ቸር መምህር፡ የዘላለምን ሕይወት እንድወርሰ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው፡**
>
> **ኢየሱስም፡ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ፡ ከእግዚአብሔር በቀር፡ ቸር፡ ማንም የለም።**
>
> **ትእዛዛቱን ታውቃለህ፡ አታመንዝር፡ አትግደል፡ አትሰረቅ፡ በሐሰት አትመሰክር፡ አባትህንና እናትህን እ... እክብር አለው።**
>
> **እርሱም፡ ይ... ይህን** ሁሉ፡ ከሕፃንነቴ **ጀምሬ፡** ጠብቄአለሁ **አለ።**
>
> **ኢየሱስም፡ ይህን ሰምቶ፡ አንዲት ገና ቀርታሃለች፡ ያ... ያለህን** ሁሉ፡ **ሸጠህ ለድሆች ሰጥ፡... በሰማይም** መዝገብ **ታገኛለህ፡ መጥተህም፡... ተከተለኝ አለው።**

30 የፈለግኩት፡ **መጥተህም፡ ተከተለኝ፡** የሚለውን ቃል ነው፡ ይህ ለአስር ሺህ ልጆች ብናገር ወይስ ለራሴ ብናገር፡ ልሰጣቸው የምችለው ምርጥ ምክር ይህ ነው። ትእዛዝ ነው፡ ለማንም ሰው በተለይም ለወጣቶች፡ የተሰጠ ታላቅ ነገር ነው ብዬ አሰባለው፡ "ተከተለኝ።"

31 የሆነ ሰው ትከተላላችሁ። አሁን፡ ያ... ያንን ማስታወስ ትችላላችሁ። የሆነ ሰው ትከተላላችሁ። ያንን ሰው የምትከተሉበት መንገድ፡ የምትከተሉት ሰው የሚከተለው ማንን እንደሆነ፡ እርግጠኞች ሁኑ። እ... እያችሁ?

32 ጳውሎስ በአንድ ወቅት፡ "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉኝ፡" አለ። በሌላ አነጋገር "እኔ ክርስቶስን እንደምከተል፡ እናንተም ተከተሉኝ፡" ማለት ነው።

33 አሁንም፡ በዚህ በለውጡ ሰዓት፡ ሁላችንም በምንቀየርበት በዚህ— በህይወት ደረጃ ላይ። ብዙ ጊዜም **ሪኪ፡ ሪኬታ፡** እና ሌሎች ነገሮችን እያልኩ ስጮኽ ሰምታችኋል። ዘመኑ፡ ነው። እየኖርን ያለንበት ዘመን ነው። በእውነት እነዚያ ሰዎች አይደሉም ዘመኑ ነው።

34 እነዚያ ሰዎች እንደ እኛ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ወጣቶች ባለ ከባድ ጉልበት መኪኖች ይዘው፡ ወደላይ-እና-ታች በጐዳናው ላይ እየነዱ፡ እዚያ ባሉበትም ሲጋራ ያጨሳሉ፡ መጠጥ ይጠጣሉ፡ ልጃገረዶችም ሥነ ምግባር በጐደለው ልብስ፡ ነግሮችን ያደርጋሉ፡ እንደ እኛ ግን ሴቶች እና ወንዶች ናቸው። እያችሁ? ሰዎች ናቸው። ያፈቅራሉ። ይበላሉ። ይጠጣሉ። ይተኛሉ። ይተነፍሳሉ። ይሞታሉ። ልክ እንደ እኛ ሰዎች ናቸው። በዚህ ሁሉ ግን...

35 በክፉ መንፈስ ተይዘዋል። አያውቁትምም። የዚህ ምክንያት—ሰዎቹ አይደሉም፡ ነገር ግን ምክንያቱም፡ አንዳንዴ፡ የተከተሉአቸው አንዳንድ መሪዎች በተሳሳተ መንገድ ስለመሯቸው ነው።

36 አሁን፡ እናንተ ሴቶች እና ወንዶች ከዚህ የተሻለ ነገር ታውቃላችሁ። ታውቃላችሁ። ከዚህ የተሻለ ነገር ተምራችኋል። እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከመፈጸም ይልቅ፡ የተሻሉ ወላጆችና ጥሩ ስልጠና አላችሁ። የበለጠ ታውቃላችሁ።

37 እነርሱ ግን አያደርጉትም፡ እያችሁ፡ ምክንያቱም የሚሄዱባቸው ቸርቾች ዘመናዊ ቸርቾች ናቸው፡ የዘመኑ፡ የሚፈልጉት፡ ለ—ለዛሬ ብቻ ታዋቂ ሆነው ለመኖር ነው። እና፡ ኦህ፡ ማይ! ስነ ምግባር የምንለው... ለእነርሱ አቅም ይሆንባቸዋል። እያችሁ? እ... አንድ ጊዜ፡ በቅርብ ጊዜ፡ እዚህ ስለ ሰዶምና ገሞራ፡ ባየሁት ድራማ ላይ፡ እንደተናገርኩት፡ ክፉ መንፈስ-ያደረባት ሴት ሎ—ሎጥን "አንተ ሥነ ምግባር የጐደለው የምትለውን፡ እኔ አቅም እለዋለሁ፡" ትለዋለች።

38 ኢየሱስም "በኖኅ ዘመን እንደ ነበረ፡ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል፡" አለ። ስለዚህ እንደገና ወደዚያ ቦታ ተመልሰናል።

39 እስቲ ያነበብነው ይህን ሰው፡ ለጥቂት ደቂቃዎች፡ እንመልከት። ይህ ሰው እንደ እናንተ ልጆች፡ በጥሩ ቤተሰብ እንደተወለደ ምንም ጥርጥር የለውም። ያደገው ከጥሩ ወላጆች ጋር ነው። ምክንያቱም፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ባቀረበለት ጊዜ፡ አረጋግጧል። "እነዚህን ከሕፃንነቴ ጀምሮ ጠብቄአቸዋለሁ፡" አለ። ይህ የ—የሚያሳየው— ትክክለኛ አስተዳደግ እንዳደገ ነው። እንዲሁ ዝም ብሎ-ያደገ አይደለም። ታውቃላችሁ ልጆች፡ ልክ እንደናንተ፡ ትክክለኛ የ—የሆነውን ነገር ለማወቅ ያደገው ሰው ነው። ምናልባትም እግዚአብሔርን የሚፈሩ-ወላጆቹ፡ በ—በ—በልጅነቱ፡ ያስተማሩት ሊሆን ይችላል። መልካም፡ ያ ጥሩ ነው።

40 ምናልባትም፡ ገና ሕፃን ሳለ፡ እናቱ አንድ ቀን ታላቅ ሰው እንዲሆን ከፍተኛ ምኞት ነበራት። አባቱ እሱን ትምህርት ቤት የሚልክበትና፡ ጥሩ የ—የትምህርት ደረጃ የሚማርበት... በዓለም ላይ የሆነ ነገር እንዲሆን የሚያስችለው ትምህርት የሚሰጥበት ገንዘብ ነበረው። በእናቱ እና በአባቱ ቅንነት፡ ይህንን ልጅ በማስተማራቸው ምክንያት፡ ምናልባትም ልክ እንደ እናንተ ወደ ምርቃት ጊዜው አድርሰውታል፡ በትምህርት ውስጥ ያለፈበትና ትምህርቱን የተማረበትን ጊዜ፡ እያችሁ። የእናቱ እና የአባቱ ሕይወት ኩራትና ደስታ እንደነበረ ጥርጥር የ—የለውም። ምንም ጥርጥር የለውም፡ ልክ እናንተ መኪና እንዳላችሁ፡ በእነዚያ ቀናት፡ ጥሩ ፈረሶች ነበሩት፡ ልክ እናንተ ጥሩ እናት እና አባት እንዳላችሁ እርሱም

ነበሩት፡ ይንከባከቡታል፡ እናንተ ጥሩ ልብስ፡ እና መኪና—አላችሁ፡ ልክ እናንተ ዛሬ ያ... ያላችሁ ነገር እርሱም ነበረው፡ በቃ በሕይወት የሚደሰት ነበር።

41 አባቱና እናቱ ደግሞ ስለ ልጃቸው... ሳያቋርጡ ይጸልዩለት ነበር ይህም—ልጃቸው ተራ ሰው እንዳይሆን፡ ልዩ ሰው እንዲሆንላቸው ነው። ወላጆች ሁሉ ይህን ይፈልጋሉ። ኢየሱስ፡ "አባትህንና እናትህን አክብር፡" የሚለውን ትእዛዝ ጠቅሶ እንደጨረሰ ሰምታችኋል? እያችሁ? ይህም የማንኛውም ወላጅ ምኞት ነው፡ ለልጆቻቸው፡ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ፡ ማስተማር፡ ምናልባትም እነሱ ማግኘት ያልቻሉትን ነገሮች እንዲያገኙ ማድረግ። እኔም ለልጆቼ የሚሰማኝ ስሜት ይህ ነው።

42 አሁን፡ አንዳንድ ጊዜ፡ ወደ ትምህርት ቤት ስለመሄድ፡ አስባለውና፣ ቤኪን፡ ሣራን እና ጆሴፍን ይህ ሁሉ ነገር ወደ-ሚሆንበት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ነገሮች፡ እንዴት እልካቸዋለሁ ብዬ አስባለሁ? ይዤያቸው ወደ ተራራ ውስጄ፡ ልክ—እንደ ህንዳዊያን እዚያ ተራራው ላይ ላ... ላሳድጋቸው ብዬ አስባለው።

43 እውነታው ግን ይህ ነው። በልጁ ውስጥ ያለው እውነታ ሁሉ መውጣቱ አይቀርም። የትም ይሁን የት፡ የልጁ ማንነት፡ ከውስጡ ይገለጣል። ውስጡ መጥፎ ነገር ካለ፡ በሕንድ ካምፕ ውስጥ ቢኖርም እንኳ ይገለጣል። ከውስጡ ጥሩ ነገር ካለ፡ በማንኛውም ካምፕ ውስጥ ይገለጣል። እያችሁ? ስለዚህ ቁምነገሩ ከልጁ ውስጥ ምን አለ ነው፡ የልጁ የውስጥ-ሰብዕና፡ ውስጣችሁ ወሳኝነት አለው። አሁን ያላችሁበት ሁኔታ ምናልባትም በቀሪው የሕይወታችሁ ዘመን የምትኖሩበት ሁኔታ ሊሆን ይችላል። እየተለወጣችሁ ነው።

44 ይህ እንደሆነ ታውቃላችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚከተሉት ሰዎች መካከል ስማንያ-ሰድሰት በመቶ የሚሆኑት ሃያ-አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ይከተሉታል። ይህ ማሳያ ነው። አሃዛዊ መረጃዎች የሚያሳየው ይህን ነው። ሰማንያ-ሰድሰት በመቶ የሚሆኑት ወደ ክርስቶስ የሚመጡት፡ ሃያ-አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ነው። እናንተ፡ ይህን ዕድሜ ካለፋችሁ በኋላ፡ በገዛ መንገዳችሁ ትቀረጻላችሁ ወይም ትገባላችሁ። ኦህ፡ እርግጥ ነው፡ ይቻላል። ሰባ፡ ሰማንያ፡ ዓመት ሲሞላቸውም፡ ወደ ጌታ ይመጣሉ፡ ግን አልፎ አልፎ ነው። እያችሁ?

45 ወጣት ስትሆኑ ማንነታችሁን ትገነባላችሁ። ምኞታቹሁን ማድረግ በምትፈልጉት፡ እና በሕይወት ውስጥ ለማሳካት በምትሞክሩት ነገሮች ላይ ታደርጋላችሁ። ስለዛ ታስባላችሁ። ስታስቡ፡ እርግጥ ነው፡ አዕምሯችሁ ውስጥ፡ ወደ አዕምሯችሁ የሚመጣው በሆነ በማይታወቅ አዕምሯችሁን በ—በሚቆጣጠር ነገር ነው። ከዚያም ወደ አዕምሯችሁ ውስጥ በሚመጣበት ጊዜ፡ ከዚያ ትናገራላችሁ፡ ያንን ታደርጋላችሁ። ከዚያም ምኞታችሁ ወደዚያ ይሰባችኋል።

46 ስለዚህ፡ እናቱና አባቱ፡ ይህ ወጣት ትልቅ ምኞት እንዳለውና... ይህንንም ለማሳካት የሚያስችል፣ በቂ ገንዘብ እንዲኖረው ይጠብቃሉ። ከዚያም፡ ይህ ወጣት ያንን አ—አጋጣሚ እንዲያገኝ፡ እንደጸለዩለት ምንም—ጥርጥር የለውም። እያችሁ፡ ማድረግ የ—የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል። ምናልባት ጥሩ ፈረሶች ነበሩት፡ ም—ምናልባትም በሴቶች መካከል በጣም የታወቀ ሰው ነበር።

47 በወንዶች ላይ የሚሆነው፡ በሴቶችም ይሆናል፡ የአንዱ በተቃራኒውም ይሆናል፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም ስለ ሰው ሕይወት፡ ስለ ነፍስ፡ ስለ ወንዶችና ሴቶች እየተነጋገርን ነው።

48 ከዚያም፡ ልጁ ከነበረው ከዚህ ሁሉ ጥሩ አጋጣሚ በኋላ፡ አያችሁ፡ "ቀላል ጎዳና፡" ብለን በምንጠራው አይነት ህይወት መኖር ጀመረ፡ በጣም ብዙ መጨነቅ በሌለበት ቦታ ላይ ሆነ። ወላጆቹ ገንዘብ ነበራቸው። ገ... ገ... ድንቅ ገዥ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ ላይ የሚያመላክተው፡ እንደ... ሀብታም፡ እንደ ወጣት ገዥ ነው። እንዳየነውም... በወጣትነቱ፡ ምናልባትም በአሰራዎቹ ዕድሜው፡ ገና ከትምህርት ቤት እንደወጣ፡ ገና እንደተመረቀ፡ ምናልባትም ከጥቂት ሳምንታት በፊት፡ ወይም የሆነ ነገር፡ እንዲህ ሆነ... ገዥ ነው፡ ልብ የሚመኘውን ነገር ሁሉ አገኘ።

49 ልጁም ዘመናዊ ሪኪ አልነበረም። ጥሩ ልጅ ነው። ሉቃስ ስለዚህ ጉዳዩ ሲጽፍ፡ ወይም ማርቆስ፡ ይመስለኛል፡ ኢየሱስ ወደ እርሱ ተመልክቶ ተነፈሰ፡ ምክንያቱም፡ ወዶት ነበርና። አያችሁ? ስለ ልጁ የሆነ ነገር አለ። ከዚህ ልጅ ጋር የተሳሰረ አንድ ጥሩ ሰብእና ነበር። የመጣው ከየት ነው? የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ካስተማሩት፡ እና እንዲጠብቃቸው ካደረጉት ከጥሩ ቤተሰብ። ከልጅነቱ ጀምሮም፡ ጠበቀው።

50 ልጁም ምኞት ነበረው፥ ዘላለማዊ ሕይወትን ይፈልግ ነበር። እርሱም እንዲህ አለ፡ "ቸር መምህር ሆይ፡ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ላድርግ?"

51 አያችሁ፡ በዓለም ላይ ካሉት ነገሮች ሁሉ፡ ውስጣዊ ነፍሳችሁ ያላገኛችሁት፡ የምትፈልጉት ነገር እንዳለ ትነግራችኋለች። በሀብት ብቻ... ወይም፡ ሁልጊዜ ሀብት መሆን አይጠበቅበትም። ዝና፡ ሊሆን ይችላል፡ አንዲት ቈንጆ ልጃገረድ፡ ከአቅም በላይ ውበት ሊኖራት ይችላል። ምናልባት በትምህርት ቤት ውስጥ በጣም ታዋቂ ነች። ምናልባትም ልጁ የፈለገውን ልጃገረድ ማግኘት ይችላል። ደህንነቱ የተጠበቀ ይመስለዋል። ይህ ደኅንነት አይደለም። ይህ ልክ እንደ ሜዳ አበባ ይጠፋል። አያችሁ? ይሄዳል። ግን ብዙም አይቆይም። ጥቂት ጸሃይ ትመታለች፡ ትጠፋለች፡ ከዚያ ለዘለአለም መኖር ያለባት ነፍስ ይዛችሁ ትቀራላችሁ።

52 ይህም ወጣት ልጅ ጥሩ ሰብእና ነበረው፡ ምክንያቱም ራሱን ለጌታ ኢየሱስ ያቀረበው፡ በጉልበቱ ተንበርክኮ መሆኑን እያወቀ ነው። እንዲህ አለ፡ "ቸር መምህር ሆይ፡ የዘላለምን ሕይወት አገኝ ዘንድ ምን ላድርግ?"

53 እርሱም እንዲህ አለው፡ "ስለ ምን ቸር ትለኛለህ፡" እንዲህ አለ፡ "ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር፡ ቸር እንደሌለ እያወቅህ?" አያችሁ? እዚህ ላይ ወጣቱ ሰው የገለጸው ነገር ምንድን ነው? እግዚአብሔር ስለ መሆኑ። አያችሁ? እርሱም እንዲህ አለ "ትእዛዛቱን ታውቃለህ፡ ጠብቃቸው፡" አለው።

እንዲህ አለ፡ ስለዚህ እንዲህ አለ፡ "መምህር ሆይ፡ የትኞቹ ትእዛዛት ናቸው?"

54 "'አባትህንና እናትህን አክብር፡' እና የመሳሰሉት ትእዛዛትን ነው፡" አለው።

55 እንዲህ አለ፡ “ከሕፃንነቴ ጀምሮ፡ ይህን አድርጌአለሁ። አየህ፡ ይህን አድርጌአለሁ።”

56 ኢየሱስም “አሁንም አንድ ነገር ይጎድልሃል። ሂድና፡ ያለህን ሁሉ ሸጠህ፡ ለድሆች ስጥ፡ ከዚያም ተከተለኝ፡” አለው።

57 እንዴት ያለ እድል ነው! ጴጥሮስ፡ ያዕቆብ፡ ወይም ዮሐንስ፡ ከእነዚህ አንዱ ቢሆን ኖሮ። አያችሁ፡ ልጁ ተምሮ በትክክል ያደገ፡ ክርስቶስ እንዲጠቀምበትም፡ በፊቱ አቀረቡት ምናልባትም የተማረ፡ ወጣት፡ ሀብታም፡ ተጽዕኖ ያለው፡ ወንጌልን ሊያቀርብ በሚችልበት፡ ቦታ ሁሉ እንዲጠቀምበት፡ በክርስቶስ ፊት ቀርቦ ነበር፡ ያንን ሁሉ ግን ውድቅ አድርጎታል። ይህ ለወጣቱ ልጅ እንዴት ያለ ድንገተኛ—እርምጃ ነበር! አያችሁ?

58 “ተከተለኝ።” አሁን፡ አያችሁ፡ የሆነ ሰው መከተል ነበረበት። አሁን አብረውት የነበሩትን ሰዎች ተጽዕኖ መከተል ነበረበት፡ የአንዲት ወጣት ሴት ተጽዕኖ፡ አብረውት የነበሩትን የወንዶች ቡድን ተጽዕኖ፡ በትምህርት ቤት የነበሩትን፡ የሥራ ባልደረቦቹን ተጽዕኖ መከተል ነበረበት፡ ወይም ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ነበረበት። በመልካምነቱ ሁሉ፡ የዘላለም ሕይወት እንደሌለው ያውቅ ነበር።

ልጆቼ፡ ልታስቡበት የሚገባው ነገር ይህ ነው። አያችሁ?

59 ዛሬ ማታ ልጁን ተመልከቱት፡ ምን ሊሆን ይችል እንደነበር፡ ምን እንደ ሆነ፡ ዛሬ ማታ የት ሊኖር እንደሚችል አሰቡት። በሆነ ቦታ ውስጥ ነው። እሱም ሰው ነበር። በሆነ ቦታ ውስጥ ነው። ፍርድ በመጠባበቅ ላይ ነው። በዚያ ቀን የፍርድ ቀን ለመጋፈጥ በመጠባበቅ ላይ ነው፡ ያንኑ እድል አለመቀበል ለእናንተም ልጆች ቀርቦላቹኋል፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ማለት ይቻላል፣ ጥሩ ልጆች፡ ጥሩ ሰብእና፡ ጥሩ አባቶች እና እናቶች፡ ያላችሁ ነገር፡ ካልፈለጋችሁ በስተቀር መሥራት እንኳን አይጠበቅባችሁም። አያችሁ?

60 ነገር ግን ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ ሌላም ነገር አለ። ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ ነገር አለ። ይህ ቃል፡ ዛሬ ማታ፡ ፈጽሞ አይሞትም። አሁንም ቢሆን ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ፡ ለእያንዳንዱ ወጣት ሴት ፈታኝ ነው፡ “ተከተለኝ።” አያችሁ?

61 ቃላቶች አይሞቱም። ማንኛውንም ነገር በምትናገሩበት ጊዜ፡ አስታውሱ፡ በመኪናዋ ውስጥ በሰውር ይሁን፡ በመድረክ ላይ ይሁን፡ ከወዳጅዋ ወይም ከሴት ጓደኛዋ ጋር በጎዳና ጥግ ላይ ይሁን፡ የትም ይሁን የት፡ ቃል መቼም አይሞትም። ለ—ለዘላለም ይኖራል።

62 ያቺን ልጅ ሳያት… በቀደም በሌሊት በራእይ ያየኋትን፡ ቄንጆ፡ ወጣት የሆሊዉድ ተዋናይ፡ ሰትሞት አይቻታለሁ፡ ልትሞት ሰትል፡ እርዳታ ለማግኘት ስትሞክር አይቻታለሁ። ሚስ ሞንሮ፡ በልብ ድካም ነው የሞተችው። ከሁለት ዓመት በፊት ነበር፡ ሰትሞት አይቻታለሁ። ከሁለት ቀን በኋላ ሞተች።

63 ከዚያም፡ በቀደም ምሽት፡ የልጅቷን ድምፅ ሰማሁ። እንዴት? ልጆች እያጫወቱኝ ነበር፡ “አባዬ፡ አንተ'ኮ ሁል ጊዜ፡ መመለሻ ወደሌለበት ወንዝ ደጋግመህ ሄደህበታል።” “ዛሬ ማታ፡ እንደዚያ ዓይነት ይታያል፡” አሉ። አንድ ወይም ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ፡ አንድ ምሽት እንደሚታይ ነግረውኛ ነበር።

“እሺ፡ ይሄን ማየት እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም በዚህ ወንዝ ላይ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ተጉዣለሁ፡ አምስት ጊዜ፡ ይመስለኛል፡” ብዬ አሰብኩ። መልካም፡ ላየው ፈ—ፈለግኩ።

64 ወይዘሮ ሜሪሊን ሞንሮ የተወነችው ነው። መልካም፡ ያቺ በራዕይ ያየኋት ልጅ ነበረች። **መመለሻ የሌለበት ወንዝ** በሚለው ትወናዋ፡ በፎቶው፡ እና በትወናው፡ ላይ ነበረች፡ ያንን ስትቀረጽ፡ ምናልባት ከአሥራ አምስት ዓመት በፊት ሊሆን ይችላል። የቆየ ቀረጻ ነበር፡ ምናልባት ከሃያ አመታት በፊት። ከሞተች ሁለት ዓመት ሆኗታል። ግን ይሄው እሷ በድጋሜ፡ በሕይወት፡ እያንዳንዷ ድርጊት እና እያንዳንዱ ቃል። አያችሁ? ስራዋ እንደገና ሕያው እስከሚሆን ድረስ አሁንም በማግኔቲክ ቴፕ ላይ ተቀድቶ አለ።

65 ይህ ብቻ አይደለም፡ የምንናገረው ነገር ሁሉ ሕያው ነው። የምንናገረው ቃል ሁሉ አይሞትም። አሁን በክፍሉ ውስጥ የሚመጡት ቃላት፡ የሰዎች ቅርጾች ናቸው። ቴሌቪዥን መጎዱን ይቀበለዋል። እዚህ ላይ የምትናገሩት፡ በተመሳሳይ ሰከንድ፡ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ትሰማላችሁ። በዚህ ክፍል ውስጥ እንኳን ከመስማታችሁ በፊት፡ በዓለም ዙሪያ፡ በኤሌክትሮኒክ ይሰራጫል።

66 የእግዚአብሔር ታላቅ እስክሪንም ያንን ይቀበለዋል። የምታደርጉትን እያንዳንዱን እንቅስቃሴና እያንዳንዱን ድርጊት፡ በፍርድ ቀን ትገናኙታላችሁ። አያችሁ? ስለዚህ፡ ወጣት ሆይ፡ ቆም ብለህ፡ ስለ እነዚህ ነገሮች ማሰብህ ጥሩ ነው፡ እየህ፡ ምክንያቱም እንደገና ትገናኛቸዋለህ። አያችሁ?

67 እስቲ ይህን ወጣት እንከታተለው፡ ያገኘውን እድል እንመልከትና፡ እራሳችሁን በእሱ ቦታ አስቀምጡ። የትኛይቱም ሴት፡ ልክ እንደ ቤኪ እና እንደ ማሪሊን፡ እናንተ በእርሱ ቦታ ላይ ያው ናችሁ፡ አሁንም ያንን ህያው የሆነውን ድምጽ ልትሰሙ ትችላላችሁ።

68 አሁንም ህያው ነው። እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ሳይንስ እንዲህ ይላል፡ “ከዛሬ ሀያ ዓመት በኋላ፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የተናገረውን ቃል፡ በቃል ድምፁን ትሰማላችሁ።” አሁንም ሕያው ነው። ማዕበሏ እንደማይቆም፡ በውቅያኖስ ውስጥ እንደተወረወረች ጠጠር ነው። በሺዎች የሚቈጠሩ ኪሎ ሜትሮች ርቆ፡ ወደ ባሕሩ ዳርቻ ይሄዳል፡ ከዚያም ተመልሶ ይመለሳል።

69 አንድ ድምፅ አንዴ እንዲህ በአየር ላይ ሲነገር፡ ፈጽሞ አይጠፋም። በፍርዱ ላይ ምንም ማለት የምትችለው ነገር የለም። ቀድመውኑ እዚያው ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ በዚያ ወጣት ላይ፡ “ተከተለኝ” እያለ ይጮኻል፡ እሱም ዞር አለ፡ ወደ እስክሪኑ ሲመለከት፡ አዘነ፡ ምክንያቱም ትልቅ ንብረት ነበረው። አያችሁ? ሁልጊዜ ገንዘብ... መሆን አይጠበቅበትም። ሌሎች ነገሮችንም ሊሆኑ ይችላሉ። አያችሁ? ያንን ጥሪ ከምናደርግ በላይ የምንወደው ማንኛውም ነገር፡ አያችሁ፡ ለእኛ እንደ ገንዘብ ይሆናል። እኛን የሚያበላሽን ነገር ይሆናል።

70 አሁን ትንሽ እንከተለው። ወደ ኋላ ሲዞር ምን ሆነ? የክርስቶስን ድምፅ አልሰማም። ከጓደኞቹ ጋር ሄደ።

71 እናንተ፡ ልጆች፡ ሁላችሁም ጥሩ ልጆች ናችሁ፡ ጓደኞችም እንዳላችሁ የታወቀ ነው፡ ግን ምን ዓይነት ጓደኛ እንዳላችሁ ተመልከቱ። ጓደኛህ ክርስቶስን

እየተከተለ ከሆነ፡ አብረህ ሂድ። ክርስቶስንም፡ ተከተሉ። ካልሆነ፡ ግን አትከተሉት።

72 እስቲ እሱን እንመልከት። ጓደኞቹን ጠብቆ ሊሆን ይችላል፡ ብለን እናስባለን። ታላቅ ገዥ ሆነ። በዚያን ጊዜ ገዥ ነበር። ከጊዜ በኋላ፡ ዕቃዎቹን ለ—ለ—ለማስቀመጥ ተጨማሪ ጎተራዎችን እስከ መገንባት ድረስ በጣም የበለጸገ ሆኖ እናገኘዋለን። እርሱም ካረጀ በኋላ፡ እና የወጣት ህይወት እና የነገሮች ጭንቀት ካለፈ በኋላ፡ ለራሱ እንዲህ አለ፡ ያደረገው ነገር ሁሉ፡ ምናልባት፡ አዝናኝ ነበር።

73 እንደ እኔ፡ እንደ ባለቤቴ፡ እንደ እናቶቻችሁ፡ እንደ አባቶቻችሁ፡ በሽመገሉ ጊዜ ሊያስቡበት የሚችሉት ምንም ነገር የለም ማለት ይቻላል። አይችሉም፡ ወጥተውም—በጎዳናው ላይ-እና-ወደ ታች መሮጥ አይፈልጉም፡ ታውቃላችሁ፡ ወጣት ወንድ—እንደሚሆነው፡ ወይም ወጣት ሴቶ እንደምትሆነው አያደርጉም። ሚስቴ ማን ትሆን ባሌስ ማን ይሆን፡ ወይም፡ የፍቅር ቀጠሮዎች፡ አያችሁ፡ ያ በአእምሮአቸው ውስጥ አይኖርም። እነሱ፡ ልጆች ኣሏቸው፡ በቃ ተሞልተዋል። ነገ ካለ፡ ነገ እናንተ ሁላችሁም፡ እንዲሁ ትሆናላችሁ ማለት ነው። አያችሁ?

74 ይህን ሰው፡ ተምልከቱት፡ ምናልባት... ምናልባት አላገባም ነበር ይሆናል። እናም፡ ይሁን እንጂ፡ ታላቅ ገዥ ነበር። እርሱም...

75 በኢየሩሳሌም እንደነበረ ልማድ፡ አሁንም፡ ዛሬም፡ በሰገነት ላይ ይበላሉ፡ ቀኑ፡ ሲቀዘቅዝ፡ ምሽት ላይ ከቤት ይወጣሉ።

ከእሱም ጎን ለጎን ሌላ ገጸ ባህሪ እናያለን፥ ለማኝ የነበረ።

76 ሰውዬም፡ ባልንጀራህን—አክብር፡ ሌሎች ለአንተ የሚያደርጉልህን አንተም ለሌሎች አድርግ ከሚል ካደገበት ልምድ፡ አያችሁ፡ የክርስቶስን ጥሪ በመቃወሙ፡ በመጨረሻ... በዚህ ዓይነት ቤተሰብ ውስጥ ያደገ ልጅ ከእሱ ፈጽሞ ፈቀቅ አይልም ነበር፡ ይህ ግን ፈቀቅ አለ። ፈቀቅ አለ።

77 በዚያም አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው፡ በር ላይ ተኝቶ፡ ምግብ ከእርሱ ለማግኘት፡ በከንቱ ለመነ። ለለማኝ እንኳን ሳይሆን፡ ለውሾቹ የተጣለውን፡ ፍርፋሪ ይበላ ነበር። በቁስል ተወርሮ ነበር። ሰውየው ግን በህብረተሰቡ ውስጥ በጣም የተከበረ፡ ስለነበረ፡ ምንም ስሜት ያልነበረው ሰው ነበር። የክርስቶስን ግብዣ ውድቅ በማድረጉ፡ ደነዘዘ።

78 እና ምናልባት አንድ ምሽት፡ በዚህ ሰዓት ላይ፡ በጥሩ ወይን ጠጅ የተሞላ ብርጩቆ ቸርስ እያለ፡ ያጌጡ፡ ውብ ሴቶች፡ እና ልቡ የተመኛቸው ነገሮች ሁሉ፡ ወዘተረፈ፡ በዙሪያው ከበውት፡ ቸርስ በማለት ሳለ። በበሩ አጠገብ ለማኝ ተኝቶ ነበር።

79 በማግሥቱ ማለዳ፡ ገና ሳይነጋ፡ ሲኦል ውስጥ ተገኘ፡ አልዓዛር መጥቶ በምላሱ ላይ ውሃ እንዲያደርግ ሲጮኽ ራሱን አገኘ። ነገሩ ተቀየረ።

80 እሱም "አባታችን አብርሃም ሆይ፡" ብሎ ሲናገር፡ አስተውሉ፡ አሁንም፡ አብርሃም የአይሁድ አባት መሆኑን ትዝ አለው። እንዲህም አለ፡ "አብርሃም አባት ሆይ፡ የጣቱን ጫፍ በውሃ ነክሮ፡ ምላሴን እንዲያበርድልኝ ለማኙን አልዓዛርን ስደድልኝ። እነዚህ ነበልባሎች እያሰቃዩኝ ናቸው አለ።"

81 እርሱም እንዲህ አለ… አብርሃምም፡ በብዙ ቃላት ተናገረውና “ይህን፡ ማድረግ አልችልም፡” አለው። “ከዚህ ሁሉ ባሻገር፡ አየህ፡ በሕይወት በነበርክ ጊዜ ዕድል ነበረህ።”

82 ዕድሉን ያገኘው መቼ ነበር? ኢየሱስ፡ “ተከተለኝ” ባለው ግዜ ነው። ግን አልተቀበለውም። ገንዘብ መሰራት ወደሚችልበት መንገድ ሄደ። ያ ምንም ችግር የለውም፡ ገንዘብ ማግኘቱ ምንም ስሕተት የለውም፡ ግን እየሰራችሁ ኢየሱስን ተከተሉ። አያችሁ? እርሱ ከሕዝቡ ጋር፡ ወደ ሌላ መንገድ ሄደ።

83 ታውቃላችሁ፡ እንዲህ አለ፡ አብርሃምም እንዲህ አለ፡ “በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ፡ በአንተና በእሱ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል፡ ማንም ሰው ተሻግሮት አያውቅም፡ ወደፊትም ማንም አይሻገረውም። እዚያ ያሉት ወደዚህ መምጣት አይችሉም፡ እዚህ ያሉት ደግሞ ወደዚያ መሄድ አይችሉም። ዝግ ነው። ማንም ሰው አልተሻገረውም አይሻገርምም።”

84 ከዚያም አሁን ሰሙት። ከዚያም ወንጌላዊ መሆን ፈለገ። በወጣትነቱ፡ የ—የነፍሳት አሸናፊ፡ እንዲሆን፡ ኢየሱስ ተከተለኝ፡ ብሎ የጠራው ጥሪ፡ እንደገና ወደ እርሱ ተመለሰበት። አምስት ወንድሞች እንደነበሩትና፡ በምድር ላይ እንደደሚኖሩ፡ አስታወሰ፡ እናም ወደዚያ ቦታ እንዲገቡ አልፈለገም።

85 እርሱም “እንግዲያውስ፡ ወንድሞቼ በዚህ መንገድ እንዳይመጡ እንዲነግራቸው፡ አልዓዛርን ላከው፡” አለ። በሌላ አነጋገር፡ “‘ተከተለኝ፡’ የሚለውን ጥሪ ይቀበሉ ማለት ነው።” አያችሁ?

እሱ ግን “እነሱ፡ አይቀበሉም፡” አለው።

86 “አዎን፡ አንድ ሰው ከሞት ቢነሳና፡ ልክ እንደ አልዓዛር ያለ ሰው፡ ተመልሶ ሄዶ ቢነግራቸው ይቀበላሉ፡” አለ።

87 አያችሁ፡ ይህ የሚያሳየው፡ ከሞትን በኋላም፡ ህሊናችን ንቁ ነው። እሱ ራሱ አስታወሰ። አብርሃምም፡ “ልጄ ሆይ፡ በዘመንህ፡ ትዝ ይበልህ” አለው። አያችሁ? አሁንም ታስታውሳለህ። የማስታወስ አቅምህ አልጠፋም። አሁንም አስታውስ።

88 እናም ያ ሰው ሊኖረው የሚችለው ትዝታ፡ አሁንም በተመሳሳይ ቦታ ላይ ነበር፡ ኢየሱስ፡ “ተከተለኝ” ሲል የሰማውን አጋጣሚ ያስታውሳል። ነገር ግን የተሳሳተውን ሰው፡ የተሳሳተውን ሕዝብ ተከተለ። በተሳሳተ ሰብሰብ ውስጥ ገባ፡ የተሳሳተ ቦታም ሄደ፡ በተሳሳተ ዘላለማዊነት ውስጥ አበቃ፣ በዚያ ቀን፡ ከእግዚአብሔር ለዘላለም ይጠፋል።

89 ኢየሱስም ታላቅ አስደናቂ ቃል ተናገረ፡ “‘አንድ ሰው ከሙታን ተነሥቶ ወደ ኋላ ቢመለስም እንኳ፡ ሊያምኑ አይችሉም። ምክንያቱም የሙሴን ሕግ አላቸው፡ ይህን የማይሰሙ ከሆነ፡ አንድ ሰው ከሙታን ቢነሳም እንኳ አይሰሙም። ሊያምኑ አይችሉም።’”

90 ለምን? ለምን? ሕጉ እንዲህ ያለ ነገር ተናግሯልን? አዎን። “ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን እናንተም አድርጉላቸው።” እሱ በሕጉ ሥር ኖሯል። ነገር ግን በሩ ላይ ለማኝ እንድሞት አደረገ። አያችሁ? በ—በእግዚአብሔር ትእዛዛት ሥር ቢኖርም፡ ይህን ታላቅ የዘላለም ሕይወት ማየት አልቻለም።

91 ልጆች ሆይ፡ እናንተ፡ ሁላችሁ፡ እንደ ልጆቼ ናችሁ። ሁላችሁም፡ እንደ ወንድ ልጆቼና፡ ሴት ልጆቼ ናችሁ። በአንድ መንገድ፡ በመንፈስ፡ የምትናገሩ ናችሁ፡ አያችሁ። ይህ ትክክል ነው። ጌታ እግዚአብሔር ነፍሳችሁን በ—በአደራ ሰጥቶኛል፡ ምክንያቱም እናንተ መጥታችሁ፡ ትሰሙኛላችሁ። ታምኑኛላችሁ። አያችሁ? በአንድ በቃሉ በኩል፡ እናንተ ወንድ ልጆቼ እና ሴት ልጆቼ ናችሁ። ይህ ትክክል ነው።

92 ሁሌም አስታውሱ፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ ታላቅ ነገር ነው። ጥሩ ቤተሰብ ውስጥ ማደግ ከእግዚአብሔር የተገኘ ውርስ ነው። እንደ እናንተ ባሉ ሰብእናዎች ጥሩ ልጆች መሆን፡ ጥሩ ነገር ነው። ትምህርት ማግኘት፡ ድንቅ ነገር ነው። በዚህ ነጻ አገር ውስጥ መኖር እንኳን ድንቅ ነው። ልናመሰግንባቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉን።

93 ነገር ግን ዝም ብላችሁ የማትወርሱት አንድ ነገር አለ። መቀበል አለባችሁ። ይህም የዘላለም ሕይወት ነው። ይህንንም ማድረግ የምትችሉት ኢየሱስን በመከተል፡ ዳግመኛ-በመወለድ ተሞክሮ ብቻ ነው። ያንን ችላ አትበሉት።

94 አንድ ጊዜ ትንሽ ታሪክ ሰማሁ፡ ሰለ አንድ ሰው፡ ኦህ፡ ደሃ ነበረ። የሁልጊዜ ና—ናፍቆቱ... ትንሽ እንደተረት ያለ፡ ታሪክ ነው። ቢሆንም፡ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ተጣብቆ ይኖራል። አንድ ቀን አበባ አገኘ። እና አበባው ምትሃታዊ ነበር፡ አበባውም እንዲህ ሲል መለሰለት፡ እንዲህ አለው "በሕይወትህ ሁሉ ድሀ ነበርክ፡" አለው። "አሁን የፈለከውን ሁሉ ጠይቅ፡ ይሰጥሃል፡" አለው።

95 እርሱም "ማዶ ያለው ተራራ ተከፍቶ፡ እኔም ወደ ተራራው ገብቼ ወርቁን ማግኘት እፈልጋለሁ፡" አለ።

96 "ይሁን እሺ፡" እንዲህ አለ፡ "የትም ብትሄድ እኔን ይዘህ መሄድ አለብህ። አየህ? እኔን ከአንተ ይዘህ መሄድ ይገባል። ሰለዚህ፡ እኔ ባለሁበት ቦታ ሁሉ፡ የፈለግከውን መጠየቅ ትችላለህ።"

97 ወደ ተራራውም ሄደ፡ ተራራውም ተከፈተ፡ እሱም ወደ ውስጥ ገባ። ተረቱ እንደሚለው፡ መደርደሪያዎቹ በወርቅና በአልማዝ የተሞሉ ነበሩ። አበባውን ጠረጴዛው፡ ወይም፡ ድንጋይ—ላይ አስቀመጠው። እርሱም ሮጦ አንድ ትልቅ ዕንቍ ያዘና፡ እንዲህ አለ፡ "ይህን ለጓደኞቼ ማሳየት አለብኝ። አሁን ሀብታም ሰው ነኝ። አሁን ሁሉም ነገር አለኝ። ግዴታ ማሳየት አለብኝ።"

98 እናም አበባው ተናገረ "ነገር ግን፡" እንዲህ አለ፡ "ዋናውን ነገር ረስተሃል፡" አለው።

99 ስለዚህ ተመልሶ ይሮጠና ያነሣዋል፡ እንዲህ አለ፡ "መልካም፡ ምናልባት ከ—ከወርቅ አገኛለው። ከብር አገኛለሁ" አለ። ሰለዚህም እንዲህ አለ፡ "ምን—ያህል ሀብታም እንደሆንኩ፡ እና ያገኘሁትን ሁሉ፡ ለሰዎች ለመንገር እቾኩላለው።"

100 ወደ በሩ ሲደርስ፡ አበባው "ነገር ግን ዋነኛውን ነገር ረስተሃል፡" አለው።

101 ሰለዚህ እንደገና በፍጥነት ተመለሰ። "እዚህ ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ቁሳቁሶች ይዘናል፡" አለ። ሰለዚህ፡ ድንጋይ አነሳ። እንዲህ አለ፡ "ይሄን ድንጋይ ይዤ እሄዳለሁና፡ ተራራው ከምን ዓይነት ድንጋይ እንደተሰራ ለሰዎች

አሳያቸዋለሁ፡ ወደ ተራራው መመለሻ መንገዴ የማገኝበት ይሆንልኛል።” እያችሁ?

102 እርሱም ወደ በሩ ሊወጣ ሰል፡ አበባው፡ ለ... ለመጨረሻ ጊዜ “ዋናውን ነገር ረስተሃል፡” አለው።

“ኦህ፡” “በቃ፡ ዝም በል፡” አለው።

103 እያችሁ፡ ከዚህ በላይ መስማት አልፈለገም፡ “ዋናው ነገር ረስተሃል፡” እናም በበሩ ሮጦ ወጣ። ሮጦ ሲወጣም፡ አበባው ውስጥ ሆኖ፡ በሩ ከኋላው ተዘጋበት፡ ዋናው ነገር አበባው ነበር። እያችሁ? ዋናው ነገር አበባው ነበር።

104 ከዓመታት በፊት፡ ልጅ እያለሁ፡ እንደሁላችሁም፡ እዚህ፡ ከፊኒክስ በላይ ባለው፡ በከብት እርባታ ላይ ነበርኩ። ከአንድ ወረቀት ሰለ ማዕድን፡ እያነበብኩ ነበረ፡ ሰለ ማዕድን ቆፋሪው የተጻፈ ወረቀት። ከዚያም፡ በዚያን ጊዜ ትንሽ የአሸዋ መተላለፊያዎች ብቻ ነበሩ እንጂ፡ በዚህ በኩል መንገዶች አልነበሩም። እዚህ ውስጥ አሁንም ብዙ ማዕድን ያወጣሉ፡ ታውቃላችሁ።

105 ይህ ማዕድን ቆፋሪ ገባና፡ ብዙ ገንዘብ አገኘ፡ እና ብዙ ወርቅ ወዳለበት ደረሰ። ወደ ውስጥ ሲሄድም፡ መንገድ ላይ ባገኘው ጐጆ ውስጥ ቆየ። ከእርሱ ጋርም አንድ ውሻ ነበረው፡ እና፡ ውሻው—ከውጭ፡ ታስሮ ነበር። በዚያው ምሽት፡ ወርቁን ለማግኘት አንድ ወንጀለኛ፡ ተከትሎት ገብቶ ነበር። እርሱም ከድሮ የሰፔን ማዕድን አግኝቶ፡ ያንን ከእሱ ጋር ይዞ መጣ። ውሻውም መጮኽ ጀመረ።

106 ሰውየውም በውሻው መረበሽ አልፈለገም። “ዝም በል፡” አለው። እንዲህ አለ፡ “ነገ፡ ይህንን ይዤ፡ ወደ—ወደ ከተማ እወጣለሁ። በዚያም... የታሪኩ ሞራል ይህ ነው። “በዚያም አስመዝነዋለሁ፡ እነሆ ሀብታም ሰው እሆናለሁ። ታላላቅ መኪናዎችን እገዛለሁ። ሁሉም ዓይነት ሴቶች እና ታላላቅ መዝናኛዎች አደርጋለሁ። በጣም ውድ ነገር አግኝቼአለሁና፡ ሀብታም ሰው እሆናለሁ። ብዙ ወርቅ፡ አግኝቻለሁ።” እንዲህ አለ፡ “እኔም... ”

107 እና እንቅልፍ ለመተኛት ሲሞክር፡ ውሻው እየጮኸ ነበር፡ ምክንያቱም ውሻው፡ ማዕድን ቆፋሪው እስኪተኛ ድረስ ጠብቆ፡ አዘናግቶ የሚገባ ወንበዴ አይቶ ነበር፡

108 ዳግመኛ ተነሥቶ፡ በድጋሚ ውሻው ላይ ጮኸ፡ “ዝም በል፡” አለው። ምስኪን ውሻም ዋይ—ዋይ እያለ አደጋው እየቀረበ መሆኑን ጌታውን ለማስጠንቀቅ ሞከረ። እርሱም...

109 በሚቀጥለው ጊዜ፡ ውሻው መጮኽ ሲጀምር፡ ቆፋሪው ጠመንጃውን ያዘ። ሊረብሸው አልፈለገም፡ ሰለዚህ ተነሥቶ ውሻውን ገደለ። ወርቅ ፈላጊውም በዚያው ምሽት፡ በወንበዴው ተገደለ። የቅንጦት ሕልሞቹ ምንም አልጠቀሙትም። ለምን? የሚያስጠነቅቀውን ድምፅ ጸጥ ዝም ሰላሰባለ።

110 ምንም ነገር ለማድረግ የሞከረ ማንም አልነበረም፡ እናንተ ልጆች፡ ባደጋችሁበት መንገድ ካደጉ በኋላ፡ **የሆነ ነገር** እንዳታደርጉ ካልነገራችሁ በስተቀር፡ በ—በጭራሽ ምንም ስሕተት ማድረግ አትችሉም። አሁን፡ የሚያስጠነቅቃችሁ ድምጽ በጭራሽ ዝም አታሰኙ።

111 እና ሁሌም አስታውሱ፡ ያንን “ተከተሉኝ፡” የሚላችሁን ድምፅ ተቀበሉ፡ ሁሌም ትክክል ትሆናላችሁ። እንደምትታዘዙኝ እምናለሁ፡

እተማመንባችኋለሁ። ነገር ግን ሁሌም ኢየሱስ፡ ያ ድምፅ፡ ዛሬም በምድር ላይ ሕያው መሆኑን አስታውሱ።

112 ድምጻችን ሁሉ እና ቃል ሁሉ በአየር ሞገድ ላይ እንደሚሄድ ሁሉ፡ እንዲሁ፡ ያወራነው እያንዳንዱ ድምጽ እና ቃል ህያው ነው። እ… አያችሁ፡ እዚህ ላይ የድምጽ ማስተላለፊያ አለባችሁ። የመዕክቱ አስተላለፊያዎች እናንተ ናችሁ። መልዕክቱን የሚቀበል ጣቢያም አለ።

113 ኢየሱስም የእግዚአብሔር ቃል አስተላላፊ ነበር፡ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር ሶስትነት—በአንድ ሰው ውስጥ የተገለጠው አካል ነበር። ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነበር።

114 የእግዚአብሔርም ሶስትነት፡ የአብ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ፡ የመለኮታዊ ባህሪያት ሶስትነት፡ በዚያ አንድ ሰው፡ ማለትም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ተመሰሏል። ስለዚህ፡ በዚያ፡ እርሱ ቃል ነበር።

115 እንዲህ ብሎ የተናገረ አስተላላፊ ነበር፡ "ቃሌን ሰምቶ፡ የላከኝን የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።" አያችሁ? "እውነት እውነት እላችኋለሁ፡ ቃሌን ሰምቶ፡ የላከኝን የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።" አሁን፡ ይህ ቃሉ ከአስተላላፊው ወጣ። አንድ ቀን፡ እንዲህ አለ፡ "እውነት እላችኋለሁ፡ ይህን ተራራ 'ከዚህ ተነሥተህ ሂድ፡' ብትሉት፡ በልባችሁም ባትጠራጠሩ፡ ነገር ግን የተናገራችሁት ሁሉ እንደሚፈጸም ብታምኑ፡ የተናገራችሁትም ሁሉ ይፈጸማል።"

116 አሁን፡ ያንን ለመቀበል በውስጣችሁ ባለው በሆነ መቆጣጠሪያ፡ በእምነት፡ ጣቢያ ብቻ ብትሆኑ፡ እሱም በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ዑደት ውስጥ፡ ወደ አዲስ ልደት፡ ወደ ዳግም መወለድ ያንቀሳቅሳችኋል። አደጋ ሲመጣ ሁሌም የሚያስጠነቅቃችሁን ያንን ድምፅ ለመስማት፡ ሁሌም የተገናኛችሁ ትሆናላችሁ። ነገሮች ሲሳሳቱ፡ ስትተቱ፡ ሁሌም ማስጠንቀቂያ ይሆንላችኋል። ከዚያም፡ ልክ እንደዚያ እንደተነጋገርንበት ሀብታም ወጣት ከመሆን ይልቅ፥ እንደ ሐዋርያው ጴጥሮስ፡ ጳውሎስ፡ ወይም ለኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሳትን አሸናፊዎች ሁኑ። ልጆች ሆይ፡ እንዲሁ አድርጉ።

እንጸልይ?

117 ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ነገ ካለ፡ የነገ ወንዶችና ሴቶች፡ እና ወጣቶች እነዚህ ናቸው። ጌታ ሆይ፡ እነሱን ማሰልጠን አለብን። ነገ እንደሚኖር እነሱን ለማሰልጠን፡ ሸክም አድሮብናል። ነገ ከሌለ ግን፡ ጊዜው ዛሬ ነው።

118 ከዚያም፡ አባት ሆይ፡ በፊትህ የተከበረ ነገር እንደሌላ እናውቃለን። ሥጋ ሁሉ ክብር አልባ ነው። በትምህርትም ቢሆን፡ ምንም እንኳን እነዚህ ነገሮች ጥሩ ቢሆኑም፡ ምንም ዓይነት መልካም ሥራ፡ ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ተቋም፡ ምንም ዓይነት የሥነ ልቦና ትምህርት፡ ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ምንም ነገር እግዚአብሔርን ሊያረጋግጥ አይችልም። መሣሪያው እርሱ ነው፡ እግዚአብሔር ራሱ፡ በዘላለማዊ ሕይወት መልክ፡ ወደ እኛ እንደ ግለሰብ ሊመጣ ቻለ። ለዚህም እናመሰግነዋለን።

119 ጴጥሮስ ያንን በተናገረ ግዜ በደንብ ተገልጿል። ኢየሱስም እንዲህ አለው፡ "ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም፡ በትምህርት ቤት አልተማርከውም። ከሴሚናሪ አልተማርከውም።" የግል ነገር ነው፡ እያንዳንዱ ግለሰብ መቀበል

ያለበት ነገር ነው። “በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይቋቋሟትም፡” ብለህ ነበር። ጌታ ሆይ፡ ለዚህም እናመሰግንሃለን።

120 ይህ ድምፅ ዛሬም ሕያው ነው። አሁንም ሊቀበሉ የሚችሉ፡ የእምነት፡ ጣብያዎች፡ ሌላ ቦታ ያሉ፡ የድምጽ ጣብያዎች፡ የመልዕክት መቀበያ ጣብያዎች አሉ። ጌታ ሆይ፡ እያንዳንዳቸው እነዚህ ልጆች ይህን በልባቸው፡ እንዲቀበሉ እንጸልያለን። እንዲሁም፡ ጥሩ ለመሆን የሚያደርጉት ነገር ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን... እግዚአብሔር የሚፈርድብን በምናደርገው ሳይሆን፡ በተቀበልነው ነው። በሥራችን ሳይሆን፡ በእምነታችን ድነናል። ስለዚህ፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ ራእዩን አሁን እንዲይዙና፡ ያንን ታላቅ ዘላለማዊ ግብዣ “መጥተህም፡ ተከተለኝ” እንዲያዩና እንዲሰሙ፡ እንጸልያለን።

121 ጌታ ሆይ፡ እያንዳንዳቸው ከዓለም ነገሮች ሁሉ፡ ከዚህ ሟች፡ አስፈላጊ ካልሆነው ሕይወት፡ ይራቁ። ዛሬ ማታ እዚህ ያሉ ሁሉ፡ ከወርቃማው ፀጉራቸው፡ አንዳንዶቹ ከጥቁር ፀጉራቸው፡ ከጥቁር ዓይኖቻቸው፡ እና ከሰማያዊ ዓይኖቻቸው፡ እዚህ ሆነው እነሱ ከመቼውም ጊዜ በጣም የተሻሉ መሆናቸውን እያሳዩ ነው።

122 ታላቁ ጸሐፊ እንደተናገረው፡ “ክፉ ቀን ሳይመጣ፡ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አሰብ። ከዚያም በእነርሱ ደስ አይልህም።” ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ጴጥሮስን እንዲህ ያልከው፡ እንዴት ነው፡ “በወጣጥነትህ ጊዜ፡ ተነሥተህ ወደፈለግኸው ትሄዳለህ። ነገር ግን ስታረጅ፡ አንድ ሰው ወደማትሄድበት ይሸከምሃል።” እንዲያስታውሱት እርዳቸው፡ “ቀኑ ይህ ነውና። ጊዜውም አሁን ነው።” ይሁን፡ አባት ሆይ።

123 እያንዳንዳቸውን፡ እንደ ልጆቼ፡ እዚህ ምሽት፡ እዚህ ላለው እያንዳንዱ ልጅ እቀበላቸዋለሁ። እነሱን ለመጠበቅ፡ በእጄ ውስጥ እንዳስቀመጥክልኝ ይሰማኛል። ሁሉንም፡ ከሰይጣን እና ከሞት፡ ወደ ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ እጠይቃቸዋለሁ። አሜን።

124 ብሩካን ሁኑ፡ ልጆች። ከእናንተ ጋር ጥቂት ቃላት መናገር ደስ ይላል። እመለሳለሁ፡ ቢሊ። ጥሩ ልጆች፡ አደንቃችኋለው። ወንድም ፍሬድ፡ ጌታ ይባርክህ። ጌታ ይባርክሽ፡ እኅቴ።

63-0601 መጥተህም፡ ተከተለኝ
በቤት ውስጥ ጉባኤ
ቱሰን, አሪዞና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org